የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| | | |
|---|---|---|
| አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፸፯<br>አዲስ አበባ ሰኔ ፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 17[th] Year No.77<br>ADDIS ABABA 8[th] June, 2011 |

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፪/፪ሺ፫ ዓ.ም

ለኃይል አቅርቦት ፕሮጀክት ክፊል ማስፈፀሚያ ከኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዐቀፍ ልማት የተደረገው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ......ገጽ ፭ሺ፱፻፴፯

Proclamation No. 712/2011

OPEC Fund for International Development Fund Loan Agreement for Financing the Energy Access Project Ratification Proclamation.... Page 5937

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፪/፪ሺ፫

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዐቀፍ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለኃይል አቅርቦት ፕሮጀክት ክፊል ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፳ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር /ሃያ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዐቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ፌብርዋሪ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፩ በቪየና የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፲፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ባካሔደው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለኃይል አቅርቦት ፕሮጀክት ክፊል ማስፈፀሚያ ከኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዐቀፍ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፪/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 712/2011.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE OPEC FUND FOR INTERNATIONAL DEVELOPMENT

**WHEREAS** a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development Stipulating that the OPEC Fund for International Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of twenty million United States Dollars (USD 20,000,000) for financing the Energy Access Project was signed in Vienna, on the 23[rd] day of February 2011;

**WHEREAS** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 19[th] day of May, 2011;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "OPEC Fund for International Development Fund Loan Agreement for Financing the Energy Access Project Ratification Proclamation No.712/2011".

፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም ዐቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ፌብርዋሪ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፩ በቪየና የተፈረመው ቁጥር 1379P የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር /ሃያ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Loan Agreement No.1379 signed on the 23rd day of February 2011 at Vienna, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development is hereby ratified.

3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 20,000,000 USD (Twenty Million United States Dollars ) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. <u>Effective Date.</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of June, 2011**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት